

# ሙዝ ሻጩ ቶም


Humphreys Odunga
Zablon Alex Nguku
Dawit Girma

Amharic
Level 2



ቶም ለመብል የደረሱ ሙዞችን በቁና ተሸክሟል።



ቶም ሙዞችን ለመሸጥ ወደ ገበያ ሄደ።



ሰዎች ገበያ ውስጥ ፍራፍሬ እየገዙ ነው።



ግን የቶምን ሙዝ የሚገዛው ጠፋ። ፍራፍሬ መግዛት የሚፈልጉት ከሴቶቹ ላይ ነበር።



‹‹በኛ ማኅበረሰብ ውስጥ ፍራፍሬ የሚሸጡት ሴቶች ብቻ ናቸው›› ይላል ህዝቡ። ከዛም ‹‹ምን ዓይነት ሰው ነው ይሄ?›› ተባባሉ።



ነገር ግን ቶም በፍጹም ተስፋ አልቆረጠም።
‹‹አለች ሙዝ፤ የኔን ጣፋጭ ሙዝ ግዙ!››
እያለ መለፈፍ ጀመረ።



አንዲት ሴትዮ አንድ ጉንጉን ሙዝ ከቁናው ላይ አነሳች። ከዛም በትኩረት ተመለከተችው።



ሴትዮዋም ሙዙን ገዛች።



ከዛ ሌሎች ሰዎችም መጡ። የቶምን ሙዞች
እየገዙ መብላት ጀመሩ።



ወዲያው ቁናው ባዶ ሆነ። ቶምም ሽጦ ያገኘውን ገንዘብ ቆጠረ።



ከዚያም ቶም ሳሙና፣ ስኳርና ዳቦ ገዝቶ በቁናው ውስጥ አስቀመጠ።



ከዚያም የገዛውን ቁናው ውስጥ አድርጎ ወደቤቱ ሄደ።

# Storybooks Canada

storybookscanada.ca

## ሙዝ ሻጩ ቶም

Written by: Humphreys Odunga
Illustrated by: Zablon Alex Nguku
Translated by: Dawit Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Canada in an effort to provide children's stories in Canada's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons
Attribution 4.0 International License.